## መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ካሉት የተለያዩ ዓለማዊ መጻሕፍት ማለትም የፍልስፍና፣ የልብወለድ መጻሕፍት በጣም የተለየና በፍጡር አእምሮ የተደረሰ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ደራሲነት በቅዱሳን አባቶችጸሐፊነት የተጻፈ ነው። በውስጡ ያሉትም መንፈሳዊ ትምህርቶች ጊዜ የማይሽራቸው ምን ጊዜም የማያረጁ ዘለዓለማውያን ናቸው። ትውልድ ያልፋል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ ሰዎች አንደበት አዲስ ሆኖ ይነገራል። ሌሎች መጻሕፍት በተደጋጋሚ ሲነበቡ ይሰለቻሉ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ግን ምንጊዜም አዲስ ነው። ምስጢሩም እንደ ባሕር አሸዋ የበዛ ነው። ምክንያቱም የዘለዓለማዊው የአምላክ ቃል ነውና፤ «ትውልድ ያልፋል አንተ ግን እስከ ዘለዓለም ያው ነህ ዘመኖችህም አይወሰኑም» የዚህ ታላቅ ጌታ ሕያው ቃል ነው። ስለሆነም ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ በእርሱም የሚመሠረቱትን ሕያው ሊያደርግ ይችላል።

### ብሉይ ኪዳን

በመጀመሪያ በእብራይስጥ ቋንቋ ተጻፈ፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን የአንድ አምላክ አማኞች የሆኑትን የዕብራውያንን ታሪክ ይተርካል። በውስጡም ብዙ የተስፋ ቃሎችን የያዘ ነው። ስለመሲሁ ክርስቶስ መምጣትም የተነገሩ ትንቢቶችን በብዛት አሉበት። በ1400 ዓመተ ዓለም አካባቢ ይህም ከክርስቶስልደት በፊት መሆኑ ነው በዚያን ጊዜ እንደተጻፈ ይገመታል።

የብሉይ ኪዳን ጻሕፍት በብዛት አርባ ሲሆኑ ከእነሱም ውስጥ አምስቱን ኦሪት የጻፈው ታላቁ ነቢይ ሙሴ ነው። በ284 ዓ.ዓ ከክርስቶስ ልደት በፊት በጥሊሞስ በተባለው ንጉሥ የንግሥና ዘመን ብሉይ ኪዳንከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ቋንቋ ተተረጐመ። ከዚያም በሄሮዲሞስ ዘመነ መንግሥት (366 ዓ.ም) ጀሮም የተባለው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ወደ ላቲን ቋንቋ ተረጐመው።

ብሉይ ኪዳን በሀገራችን ቋንቋ በግእዝ የተተረጐመው ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ሲሆን ይኸውም በንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው።

### ሐዲስ ኪዳን

ስለመሲሐ ክርስቶስ መወለድ በዚህች ምድር ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር መመላለስ፣ መሞትእንዲሁም ድል አድርጐ መነሣት፣ ማረግ የመሳሰሉትን የሚያስረዳ ሲሆን የተጻፈው ከ48-98 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆን ይገመታል።

የሐዲስ ኪዳን ጻሕፍት ብዛታቸው ስምንት ሲሆን ከእነሱም ውስጥ ብዙዎቹ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ የተማሩ፣ በዋለበት የዋሉ፣ ባደረበት ያደሩ ነበሩ። ስለዚህ ጌታ ራሱን በዓይናቸው አይተው፣ በጆሮአቸው ሰምተው፣ በእጃቸው ዳስሰው የጻፉ ናቸው። ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ጻሕፍት ለየት ያሉ ናቸው።

### አራቱ ወንጌላውያን

ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ በመባል ይጠራሉ። ማቴዎስና ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ውስጥ ሲሆኑ፤ ማርቆስና ሉቃስ ሉቃስ ደግሞ ከሰባ አርድእት ውስጥ ናቸው። ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ከአርድእት የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው? ቢባል ጌታ ወንጌሉን ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፉት ቢያደርግ ኖሮ አርድእት ለማስተማር ሲወጡ እናንተንማ ማን ይሰማችኋል፤ የውጭ ሰው ናችሁ የውስጥማሰዎች ብትሆኑ ወንጌልን በጻፋችሁ ነበር ብለው አይሁድ ትምህርታቸውን ከመቀበል ወደ ኋላ ባሉ ነበር። ስለዚህ ጌታ ይህን አስቀድሞ ስለሚያውቅ ከአርድእትም ወንጌልን እንዲጽፉ አደረገ። እንዲሁም ደግሞ ሐዋርያት ብቻ ጨርሰው ቢጽፉት ኖሮ የአርድእት ክብር በአይሁድ ዘንድ ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ ባልታወቀ ነበር። አሁን ግን አርድእትም በጌታ ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን ወንጌልን በማጻፉ ታወቀ።

አርድእት ብቻስ ለምን አልጻፉትም  ሁለቱ ከሐዋርያት ስለምን አደረገ? የሚል ጥያቄ በእያንዳንዳችን ሕሊና ሊቀረጽ ይችላል። ለዚህም ምክንያት አለ። ይህ የሆነበት ምክንያት ስለ ወንጌል ክብር ነው። በአጠቃላይ ወንጌል በአርድእት ብቻ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ይህችማ ተርታ ሕግ ናት፤ ደግቲቱ ሕግ ምስጢረመንግሥትን በደብረ ታቦር፣ ምስጢረ ምጽአትን በደብረ ዘይት፣ ምስጢረ ጸሎትን በጌቴ ሴማኒ ባዩ አእማደ ምድር በተባሉ በልበ ሐዋርያት ቀርታለች በማለት አይሁድ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌል ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና።

## ስለሌሎች የሐዲስ ኪዳን ጸሕፍት

<u>ጳውሎስ</u>፤ የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ቅዱስ ጳውሎስ ከብንያም ነገድ እንደሆነና ዳሩ ግን ዜግነቱ ሮማዊ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው እውነታ ነው። ጳውሎስ ለአይሁዳውያን ወገኖቹ ትውልዱ አይሁዳዊ መሆኑን ሲገልጽ (እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ በዚች ከተማበገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ፣ የአባቶቻችን ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ፣ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ) የሐዋ.ሥራ 22፤3-5።  እንዲሁም ደግሞ በዜግነት ሮማዊ መሆኑን ሲገልጽ «የሮሜን ሰው ያለፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን?» የመቶ አለቃውም በሰማ ጊዜ ወደ ሻለቃው ቀርቦ ይህ ሰው ሮማዊ ነውና ታደርገው ዘንድ ካለህ ተጠበቅ ብሎ ነገረው። ሻለቃው ቀርቦ «አንተ ሮማዊ ነህን? ንገረኝ አለው፤ እርሱም አዎን አለው። ሻለቃው መልሶ እኔይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት አለ። ጳውሎስም እኔ በእርስዋ ተወለድሁ አለው። ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ። ሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ አሳስሮት ነበርና።

ጳውሎስ የመጀመሪያ ስሙ ሳውል ነበር፤ በመጀመሪያ ለኦሪት እምነት ቀናኢ የነበረ ሰው ስለነበር ከአይሁዶች ጋር ሆኖ ክርስቶስን ያሰቃየ፤ እንዲያውም ጌታን በእርግጫ ሲመታው ጌታም ወደኋላው ዞር ብሎ «ሳውል መመለስህ ሳይቀር ለምን ትረግጠኛለህ?» ቢለው ለኦሪት እምነት ቀናኢ ነበርና እንዴት ደፍረህ እኔን እንደዚህ ትለኛለህ? ብሎ ተጨማሪ ጅራፍ አስገርፎታል። እንዲሁም ከጌታ ሞትና እርገት በኋላ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ለስብከት በተሰማሩበት ወቅት የክርስቶስ ወገኖች የሆኑትን ሁሉ በዋሉበት ለማጥፋት ከሊቃነ ካህናቱ ዘንድ የፈቃድ ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ሳለ ደማስቆ በተባለችው ቦታ ላይ ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያው አንጸባረቀ፤ የብርሃን ጐርፍ በዙሪያው ጐረፈ። ጳውሎስም ደንግጦ ወደቀ። «ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ፣ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ላንተ ይብስብሃል» አለው ጌታ። ጳውሎስም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አመነ፤ ከዚያ በኋላ ምርጥ ዕቃነቱን በተግባር አስመሰከረ።

ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋቸው መንፈሳዊ መልእክቶች አሥራ አራት ናቸው። በመጨረሻም በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት የሰይፍ ከረባት በአንገቱ ላይ ያሰረ ታላቅ የሃይማኖት አባት ነው።

### ቅዱስ ጴጥሮስ

የዮና ልጅ ስምዖን ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር አሣ ከሚያጠምድበት ከባሕር ዳር እንደተጠራና «በወንጌል መረብነት ሰውን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ» ብሎ ጌታ እንዳስከተላቸው ማቴዎስ ጽፎታል (ማቴ.4፤18-21)። ቅዱስ ጴጥሮስ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በቂሣርያ የመሰከረና በጌታም ዘንድ ብፁዕ ነህ ተብሎ የተመሰገነ ነው። እርሱም እንደ ጳውሎስ በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት በሮም አደባባይየቁልቁሊት የተሰቀለው። ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለት መልእክታትን ጽፏል።

### ያእቆብና ይሁዳ

ወንድማማቾች ሲሆኑ የእመቤታችን አገልጋይ የነበረው ዮሴፍ ከሚች ሚስቱ የወለዳቸው ልጆቹ ሲሆኑ ሁለቱም አንዳንድ መልእክታት ጽፈዋል።

### የመጽሐፍ ቅዱስ ብዛት

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ሰማንያ አንድ መሆኑን ትናገራለች። ዳሩ ግን በኣለም ላይ በብዛት ተሰራጭቶ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ስልሣ ስድስት ነው። በስልሣ ስድስቱ ውስጥ የሌሉት መጻሕፍት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

**ከብሉይ፤**
1/ **መጽሐፈ ሄኖክ**
2/ **መጽሐፈ ኩፋሌ**
3/**መጽሐፈ ሲራክ**
4/**መጽሐፈ እዝራ ቀዳማዊ**
5/**መጽሐፈ ዮዲት**
6/**መጽሐፈ ጦቢት**
7/**ጥበበ ሰለሞን**

**<u>ከሐዲስ ኪዳን</u>**

| | | |
|---|---|---|
| **ትእዛዘ ሲኖዶስ** | **ግሥው ሲኖዶስ** | **አብጥሊስ ሲኖዶስ** |
| **ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ** | **መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ** | **መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ** |
| **ቀሌምንጦስ** | **ዲድስቅልያ** | |

**እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ሳታጓድል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትቀበላለች። አንዳንዶች  ዘመን አመጣሽ እምነቶች ግን ከስልሣ ስድስቱ ዉጭ ሌላ የለም ሲሉ ይሰማሉ።ለዚህም የሚጠቅሱት ዮሐንስ ራእይ መጨረሻው ላይ ያለውን ቃል ፤ «ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል። ማንም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጐድል በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅዲስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጐድልበታል» ራእይ** 22፣18**።**

**ይህን አባባል በጥሞና ስናጤነው የዮሐንስ ራእይን ብቻ የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ በትንቢትመጽሐፍ አለ እንጂ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውጭ አላለም። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ከመነሻው እንደዚሁ አንድ ላይ እንደ ተጠረዘ ሆኖ የተገኘ አይደለም። ጻሕፍቱ በተለያ ዘመን የነበሩ እንደሆነ ሁሉ መጻሕፍቱም በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ ናቸው። በተለያዩ ቦታዎችም ነበሩ። እንግዲህ በአንድ ሰው እንደተጻፉና በአንድ ወቅት ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተጽፈው አልቀው በጥራዝ መልክ እንደወጡ አድርጐ በመውሰድ የዮሐንስ ራእይን ማጠቃለያ ለሁሉም መጻሕፍት አድርጐ መውሰድ አለማወቅ ወይም ተንኮል ነው።**

**ይህ ቃል የተጠቀሰበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለው። ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ያስፋፉት በቀላል እንዳልነበር ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም። በተለይ የሮም ነገሥታት ቤተ ክርስቲያን ላይ ያልመዘዙት ሰይፍ፣ ያላሳረፉት የመከራ ዱላ አልነበረም። በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች እንደ ሽንኩርት ሲቀረደዱ ቅዱሳን መጻሕፍትም የእሳት አዱኛ ተደርገው ነበር። በዚህ ወቅት ክርስቲያን ሲሞት ክርስቲያን**
**ይተካል መመሪያቸው የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ከጠፋ ግን የኋለኞቹ ክርስቲያኖች መመሪያ ያጣሉ በማለት በዋሻ በፍርክታ ውስጥ ቅዱሳ መጻሕፍት መደበቅ ጀመሩ።  ክርስቲያኖች መከራውን አሳልፈው በእግዚአብሔር ኃይል ሰላም በሰፈነበት ወቅት የተቀበሩ መጻሕፍትን ማውጣት ጀመሩ። ዳሩ ግን ቅዱሳትመጻሕፍት ውስጥ ሁሉም ሲገኙ የዮሐንስ ራእይ ግን ይጠፋል። በዚህ አዝነው ሳለ ዮሐንስ አፈወርቅ በግዞት ባለ ጊዜ ስለዚህ መጽሐፍ መቃጠል ያዝን ነበርና መንፈስ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዋርያ ፍጥሞ በተባለችው ደሴት ያየውን ራእይ አንድም ሳያስቀር ይገልጽለትና ይጽፋል። በመዝጊያውም ላይ ዮሐንስ ማስጠንቀቂያ አስፈረበት። ይኸውም ማስጠንቀቂያ «ዮሐንስ ወንጌላዊው የጻፈው ላይ እንደዚህ የሚል ነበረበት ዮሐንስ አፈወርቅ በጻፈው ላይ ግን ይህ የለበትም ወይም ደግሞ ዮሐንስ ወንጌላዊው ባየው ራእይ ላይ ይሄ አልተጻፈም በማለት ሌሎች ሰዎች በዚህ የራእይ መጻሕፍ ላይ የራሳቸውን ሐሳብ እንዳይጨምሩና እንደዚሁም እንዳይቀንሱ ተብሎ የተጻፈ የማስጠንቀቂያ ቃል ነው። ምክኒያቱም ለዮሐንስ ወንጌላዊው ያሳየው መንፈስ ቅዱስ ለዮሐንስ አፈወርቅም ምንም ሳይጨምር ሳይቀንስ ዳግመኛ እንዳሳየው ገልጾለታል።**

**እውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ወገኖች ግን ከላይ በዮሐንስ ራእይ ላይ የሰፈረውን ተገን በማድረግ ድርሳናትንና ታምራትን ገድላትን ሲነቅፉ ይታያሉ። እነዚህ መጻሕፍት ሃሳባቸውና እምነታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ አንድ ዓይነት ሃሳብና እምነትን የሚገልጹ እንጂ ባእድ አምልኮትን የሚሰብኩ አይደለም።**

**ወንጌል የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁ ነገር የለም ብላ የተናገረችውን ቃል እነዚህ መ
ጻሕፍት ተግባራዊነቱን በታሪክ አስደግፈው የሚያቀርቡ ናቸው። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት «የእግዚአብሔር
ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት
ና ለተግሣጽ ልብንም ለማቃናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል»**2**ኛ ጢሞ**. 3፣16-17**።**

**እንግዲህ ድርሳናትም ሆኑ ገድላት ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት ታላቅነት የሚገልጹ ስለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ
ያለባቸው መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። ጳውሎስ ስልሣ ስድስቱን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ተጠቀም አላለም። ገደ
ብ ሳያደርግ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው በቅዱሳን አባቶች ሆነ በሌሎች ክርስቲያኖች የተጻፉትንም መንፈሳ
ዊ መጻሕፍት አለ እንጂ።**

**ወንጌላዊው ዮሐንስም በምዕ**. 20፣30 **ላይ «ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ በሌላ መጻሕፍት የተጻፉ ብዙ ምልክ
ት ማድረጉን ገልጾአል።» ጌታ ያደረገው ሥራ ተጽፎ እንደማያልቅ አሁንም ይኸው የጌታ ሐዋርያ የሆነው ዮሐን
ስ ሲገልጽ «ኢየሱስ ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም
ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል» ዮሐ**. 21፣25**።**

**ደርሶ አዋቂ ነን ባዮች ታዲያ የጌታን የታምራቱን ሥራ ገድበው ከዚህ ውጭ ያደረገው የለም ሲሉ
ትንሽ አያፍሩም**? **የጌታ የ**33 **ዓመት ከ**3 **ወር መዋዕለ ዜና በአራቱ ወንጌላውያን ብቻ ተጽፎ የተካተተውነው ቢሉን
ማንም አያምናቸውም። እንኳን የታላቁ አምላክ የክርስቶስ ታሪክ ቀርቶ የአንድ ተራ ንጉሥታሪክ እንኳን ብዙ ቮ
ልዩም መጻሕፍት ይወጣዋል።**

**ከስልሣ ስድስቱን ውጭ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ የለም እንዳይሉ አሁንም ሌላ ማስረጃ እነሱው አምነው የተቀበሉት
መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርባቸዋል። በይሁዳ መልእክት** 1፣14-15 **«የሄኖክን ትንቢት ይሁዳ ከመጽሐፈ ሄኖክ ጠቅሶ
» ጽፎታል፤ መጽሐፈ ሄኖክ ደግሞ በስልሣ ስድስቱን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። እንግዲህ ያልተጻፈውን ከል
ቡናው አንቅቶ ሄኖክ እንዲህ ብሎ ተናገረ ብሎ ዋሸ**? **አይደለም በእውነት መሰከረ እንጂ። ይህንንም በመጽሐፈ
ሄኖክ ላይ የምናገኘው ነው መጽ**. **ሄኖክ** 1፣9**።**

**ለዚያውስ እነሱ የተለያዩ የሞት ፍልስፍና የያዙ መጻሕፍትን እየጻፉ አንብቡ እያሉ ይበትኑስ የለ**? **ታዲያ ከመጽሐ
ፍ ቅዱስ ሌላ መጻሕፍት አታንብቡ ካሉ እነሱ ሌላ መጻሕፍት እያጻፉ ያሰራጫሉ**? **ወይስ ትንቢቱ ለኦርቶዶክሳውያ
ን ብቻ ነው የተነገረው**? **ይኼ ለማጭበርበር ነውና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መጻሕፍት መርምረን እውነ
ተኛው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትን የያዙ ከሆነ አንብበን ልንረዳ ልንመራባቸው ተፈቅዶልናል። ሌላም ማስረጃ መጥ
ቀስ እንችላለን። በማቴዎስ ወንጌል** 27፣9 **ያን ጊዜ የነቢዩ ኤርምያስ ቃል ተፈጸመ እንዲህ ያለው «የእስራኤል ል
ጆች የተስማሙበትን የክቡርን ዋጋ ሠላሳውን ብር ወሰዱ» ይህን ቃል የምናገኘው በስድሣ ስድስቱ ውስጥ ሳይሆ
ን በተረፈ ኤርምያስ** 7፣2-4 **ባለው ላይ ነው።**

**እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ሐዋርያት ያስተምሩ የነበሩት ከ**46**ቱ የብሉያት መጻሕፍት እየጠቀሱ እንደነበር ነው።**

**ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጐበና በ**1992 **ካሳተሙት ላይ ነው።**